| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | መሥራች ፡ ጽሑፍ ። |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡— ሥልጡንሕዝብና ። " |
| ደራሲ ፤ | ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 1985 ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ማስታወሻ ፤ | ከ 26 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ በድጋሚ ፡ የወጣ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# መሥራች ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡— ሥልጡንሕዝብና ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

(ሥልጡንሕዝብና ፥ 3ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.005 ፥ ታኅሣሥ ፡ 1985 ፡ ዓ.ም. ።)

"ሥልጡንሕዝብና" ፡ ማለት ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ ልክ ፡ በልክ ፥ ሥልጡን ፡ ሕዝብነት ፡ ነው ። የመጣውም ፡ ሠለጠነ ፥

ሀ) ፡ ለገዢነት ፥ ተገቢነት ፣ መብት ፣ ምስፍና ፣ ችሎት ፡ አገኘ ፤

በ) ፡ ዐወቀ ፥ ተረዳ ፥ ርትዕን ፡ ተቀባይ ፣ ለፍትሕ ፡ ታዛዥ ፡ ኾነ ፤

ገ) ፡ ፈልስሞ ፡ ሠራ ፥ አከናወነ ፥ ከያኒ ፣ ኬንያ ፡ ኾነ ፤

ከሚለው ፥ ሕዝብ ፥ ጥንት ፡ በመሠረት ፥ ኀሊውን ፡ ከኀሊናው ፡ አንቅቶና ፡ በልቦናው ፡ ፀንሶ ፥ በሥሉስ ፡ ባሕርዩ ፡ አምሳል ፡ በሦስት ፡ ቀለማት ፡ አድምጦ ፥ በሦስት ፡ ኅርመት ፡ አሥርጾ ፡ ካናገረው ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ "ሠለጠ" ፡ የመጣ ፡ ነው ።

የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ባሕርዩን ፡ አልተነሣም ፥ ህልው ፡ ነው ፤ ይወልዳል ፥ ይዋለዳል ፥ ይወላለዳል ። ዘሩ ፡ "ሠለጠ" ፡ ያማርኛን ፡ አንቀጽ ፡ "ሠለጠነ"ን ፡ ወልዷል ። "ሠለጠነ"ም ፡ "ሥልጣን"ን ፡ ስም ፥ "ሥልጡን"ን ፡ ቅጽል ፡ ወልዷል ። "ሥልጡን" ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በመጋባት ፥ "ሥልጡንሕዝብና"ን ፡ ህልው ፡ ስም ፡ ወልዷል ። ውሉዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ በቀላሉ ፡ ያውቀዋል ፤ ባዕዱ ፡ አይደለም ፥ ዘመዱ ፡ ነው ። የተውሶ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የብድር ፡ ዕውቀት ፡ አይደለም ፤ የራሱ ፡ ባህል ፥ የራሱ ፡ ሥርዐት ፡ ነው ፤ አያደናግረውም ፤ ዐውቆ ፡ ይሠራበታል ፥ ወዶም ፡ ያድርበታል ።

እንግዲህ ፥ ወደተነሣኹለት ፡ ርእሰ ፡ ነገር ፡ ልመለስ ።

በሥላሴ ፡ አምሳል ፡ የተፈጠረው ፡ ነባቢ ፣ ለባዊና ፡ ሕያው ፡ ሰው ፥ የተፈጠረለትን ፡ ተግባር ፡ የማከናወን ፡ ግዳጅ ፡ በባሕርዩ ፡ እንዳለበት ፡ ኹሉ ፥ ግዳጁን ፡ የሚወጣበት ፡ ተስተካካዩ ፡ ችሎትም ፡ በዚያው ፡ ባሕርዩ ፡ ያለለት ፥ በቂውም ፡ ሀብት ፡ በብሔሩ ፡ (1) ፡ የሰፈረለት ፥ የራሱ ፡ አዛዥ ፣ ጌታ ፥ ወይም ፡ ገዥ ፣ እግዚእ ፡ ነው ። ለጕዳዩ ፡ ራሱን ፡ ያዛል ፤ ሥልጡን ፡ ነው ። ለራሱ ፡ ይታዘዛል ፤ ሥልጡን ፡ ነው ። ያስባል ፤ ያቅዳል ፤ ይሠራል ፥ ሥራውንም ፡ ይገዛል ፥ ያገምራል ፤ ሥልጡን ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ ሲያደርግ ፥ ከፈጣሪው ፡ በታች ፥ ከራሱ ፡ በቀር ፡ በማንም ፡ አይገዛ ፤ ከፈቃዱም ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ አይታዘዝ ፤ የራሱ ፡ ጌታ ፡ እኩል ፡ ሥልጡን ፣ እኩል ፡ እግዚእ ፥ ለራሱ ፡ ታዛዥ ፡ እኩል ፡ ዜጋ ፣ እኩል ፡ ሥልጡን ፡ ነው ። መሬት ፣ ውሃ ፥ እሳት ፣ ነፋስ ፡ የማይነፈጉት ፡ እኩል ፡ ባለጸጋ ፡ ነው ።

ይህን ፡ እኩልነት ፡ ጠልቶ ፥ በብጤው ፡ ላይ ፡ ልቆ ፡ ለመታየት ፡ ሲል ፡ ጌትነቱን ፡ ከፈጣሪው ፡ አምላኩ ፡ ልዕልና ፡ ላስታይ ፡ ቢል ፥ በሥጋውም ፡ በነፍሱም ፡ የማይቋቋመው ፡ መከራ ፡ እንዳይመጣበት ፡ ስለሚሠጋ ፤ ከብጤው ፡ በላይ ፡ ለመኾን ፡ ቢንጠራራ ፡ ደግሞ ፥ ከብጤው ፡ በመጋደር ፡ ክብሩን ፡ የሚያጣ ፤ ከብጤው ፡ ለመስተካከል ፡ ቢሰላ ፡ ግን ፥ ከብጤው ፡ በመተባበር ፥ ጌትነቱን ፡ የሚያስከብር ፡ መኾኑን ፡ በባሕርዩ ፡ የሚያውቅ ፡ ብልኅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሙከራውን ፡ ሳይገፋበት ፡ በቅርቡ ፡ ሊተው ፡ ይፈቅዳል ፤ ወይም ፡ ገፍቶበት ፥ ትርፉ ፡ መላው ፡ ጕዳት ፡ መኾኑን ፡ ሲያገኘው ፥ ሊተወው ፡ ይገደዳል ። መደምደሚያውን ፥ ሰው ፥ ለራሱ ፡ ጌትነት ፡ ወይም ፡ እግዚእና ፡ ሲል ፥ የብጤውን ፡ የራስ ፡ ጌትነት ፡ ያከብራል ። ሲያከብርም ፥ ብጤውን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያሠለጥነዋል ። ጌትነቱ ፡ የታወቀለትና ፡ በብጤው ፡ ላይ ፡ የሠለጠነውም ፡ ሰው ፥ ጌትነቱን ፡ ያወቀለትንና ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያሠለጠነውን ፡ ብጤውን ፥ ተራውን ፡ በጌትነቱ ፡ ሊያውቀው ፡ ወንፈሉ ፡ ያስገድደውና ፥ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያሠለጥነዋል ። ኹለቱም ፡ ሰዎች ፥ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ እኩል ፡ ሥልጡኖች ፡ ይኾናሉ ፥ ሥልጡን ፡ ሰዎችም ፡ ይባላሉ ። በነርሱው ፡ ዐይነት ፡ ሥልጡን ፡ ሰዎች ፡ በርክተው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ሲኾኑ ፥ ወይም ፡ ሲሞሉ ፥ በቅጽላቸው ፡ "ሥልጡንሕዝብ" ፡ ይባላሉ ፥ ኹነታቸውም ፡ "ሥልጡንሕዝብነት" ፡ ይባላል ፤ ዐዳራቸው ፣ አናዋራቸው ፣ ሥርዐታቸው ፡ ደግሞ ፥ በጠቅላላው ፡ "ሥልጣኔ" ፥ በተለይም ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ ይባላል ። እንሆ ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ ከዚህ ፡ ይነሣል ።

በተመጠነ ፡ አነጋገር ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡— የብጤን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በማክበር ፡ ውዴታ ፥ የራስን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በብጤ ፡ አስከብሮ ፡ መኖር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የመብትና ፡ ግዴታ ፡ ተመዛዛኝነት ፡ የሚገኘው ፡ ባሕርያዊው ፥ ብሔራዊ ፡ (2) ፣ ተወናፋይ ፡ የመነሻ ፡ ሥልጣኔ ፥ ወይም ፡ ሥልጡንሕዝብና ፥ በኹለት ፡ ፊት ፡ ገደብ ፡ እታፈፊ ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ የሰፈነ ፡ ርትዐት ፥ ወይም ፡ በፍትሕ ፡ የሚሠራ ፣ የሚያበጅና ፡ የሚያለማ ፡ የርትዕ ፡ ኀይል ፡ ነው ። በተለይም ፥ ከጐን ፡ የብጤን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፥ ከላይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዳኝነት ፥ ከታችም ፡ የሕግን ፡ ገዥነት ፡ በማክበር ፥ የራስን ፡ አስከብሮ ፡ ከመኖር ፡ የሚገኘው ፡ ኢትዮጵያዊው ፣ ባሕርያዊው ፣ ተወናፋይ ፡ የመድረሻ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ ሥልጡንሕዝብና ፥ ባራት ፡ በኩል ፡ ተመዛዝኖ ፡ በረጋ ፥ ባራት ፡ በኩል ፡ ተመጣጥኖ ፡ በታፈፈ ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ ያረፈ ፡ ሰላም ፥ ወይም ፡ ከማጥፋት ፡ የሚከለክል ፣ ከጥፋት ፡ የሚያድን ፣ ከውድቀት ፡ የሚያስነሣ ፡ ችሎት ፡ ነው ።

---

1 'ብሔር' ፡ በግእዝ ፡ 'ብሒር' ፡ (መስፋት ፡ መንጣለል ፤ መዘርጋት ፥ ሰፊ ፣ ዝርግ ፣ ወርዳም ፣ ረዥም ፡ መኾን ፥ የቦታ ፣ የመሬት ፣ የርስት ፣ የግዛት ፤ ኪ..ወ.ክ. ፥ ገ.261) ፡ ካለው ፡ አንቀጽ ፡ ይወጣል ። ወሰን ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ። ሲወሰን ፥ ለምሳሌ ፡ 'ብሔረ ፡ አሪት' ፡ ቢል ፥ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍል ፡ ያመለክታል ፤ እንዲሁም ፡ 'ብሔረ ፡ ኵሽ' ፡ ቢል ፥ የኵሽ ፡ ልጆችን ፡ ምድር ፡ ለማለት ፡ ነው ። ሳይወሰን ፡ ደግሞ ፥ ጠፈርን ፡ ጨምሮ ፥ መላው ፡ ዓለም ፣ መላው ፡ ፍጥረት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ 'እግዚአብሔር' ፡ ስንል ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፣ የዓለም ፡ ኹሉ ፡ ገዥ ፡ ማለታችን ፡ ነው ። እንደዚሁ ፥ ሣልስ ፡ ቅጽሉ ፡ 'ብሔራዊ' ፥ ሲወሰን ፡ 'ምድራዊ' ፡ (በፈረንጅኛ ፡ 'territorial') ፤ ሳይወሰን ፡ ደግሞ ፡ 'የመላ ፡ ዓለም' ፡ (በፈረንጅኛ ፡ 'universal' | 'universel') ፡ ማለት ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ 'ብሔራዊ'ን ፡ 'የመላ ፡ ዓለም' ፡ ብሎ ፡ ያነቧል ። [አዘጋጅ]

2 ጥቅሱ ፡ የሚያመለክተው ፡ መላ ፡ ዓለምን ፡ ነው ። [አዘጋጅ]


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የኔ ፡ ጥቅም ፡ ይቅደም ፤ ወይ ፡ የኔ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ይፈጸም ፡ የሚለው ፡ ለራሴ ፡ ባይነት ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የኔ ፡ ይቅደም ፥ የሌላው ፡ ይውደም ፤ የኔ ፡ እንዲፋፋ ፡ የሌላው ፡ ይጥፋ ፡ የሚለው ፡ egoism ፡ ግን ፥ ገና ፡ በመነሻው ፥ ያንዱን ፡ ፊት ፡ ገደብ ፡ ያፈረሰ ፥ የብጤን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ የሚቀንስ ፥ ጨርሶም ፡ የሚደመስስና ፥ የራስ ፡ ነጻነትና ፡ መብት ፡ መገኛ ፡ የሚኾነውን ፡ ተመዛዛኝነት ፡ ተመልሶ ፡ የሚያፈርስ ፤ መደምደሚያውን ፥ የኹሉን ፡ ሰላም ፡ የሚነሣ ፣ የሚያደፈርስ ፣ የሚያጠፋ ፡ ስእነት ፡ ([3]) ፡ ነው ።

ሰላምን ፡ የሚነሣው ፣ የሚያፈርሰው ፣ የሚያጠፋው ፡ ስእነት ፥ እጅግ ፡ የሚያርዕድ ፣ የሚያንቀጠቅጥ ፡ እቀት ፡ ሲኾን ፤ ማፍረሻ ፣ መደምሰሻ ፡ ጠባዩን ፥ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ውንብድናውን ፡ በባሕርዩ ፡ የያዘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ማፍረሱና ፡ ማጥፋቱ ፥ ወይም ፡ ሚዛኑን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ደፍቶ ፡ መውደቁና ፡ መንኰትኰቱ ፡ የማይቀርለት ፡ ዕዳው ፡ ነው ።

የሚሠራው ፣ የሚያበጀውና ፡ የሚያለማው ፡ ርትዐት ፡ ግን ፥ በዚያው ፡ አንጻር ፥ እጅግ ፡ የሚያስተማምን ፣ የሚያበረድድና ፡ የሚያዠግግን ፡ ችሎት ፡ ነው ። ችሎትም ፥ ስእነትን ፡ ስለሚደመስስ ፥ ከቶ ፡ ጥፋት ፡ አያገኘውም ❖

*(ሥልጡንሕዝብና ፥ 3ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.005 ፥ ታኅሣሥ ፡ 1985 ፡ ዓ.ም ። )*

3 ስእነት ፤ ስኡንነት ፥ እቀት ፥ አለመቻል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።